በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጡት ምላሾች

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ **ሰኔ 1 ቀን 2012** በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው ከምክር ቤት አባላት በወቅታዊና የመንግስት አቅጣጫ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል። ዋና ዋናዎቹ ነጥቦችም ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፤

**የኮሮና ቫይረስ መከላከልና ኢከኖሚያዊ ጫናውን ለመቋቋም እየተደረገ ያለ ጥረት፡-**
የኮሮና ቫይረስ ዓለምን እኩል ያነጋገረ በሽታ ነው፡፡ 7 ሚሊዮን ህዝብ አጥቅቷል፡፡ 4መቶ ሺህ ቀጥፏል፡፡ 185 ሺህ ሰው በአፍሪካ ተይዟል፡፡ 5 ሺህ ሰው ህይወቱ አልፏል፡፡ በምስራቅ አፍሪካ 18 ሺህ ሰዎች ተይዘዋል ፡፡ በኛም አገር በሁሉም ክልሎች እና በሁለቱም ከተማ አስተዳደሮች ቫይረሱ ተገኝቷል፡፡ በዓለማቀፍ ደረጃ የአቅርቦት እና ፍላጎት አዙሪት ቀውስ ፈጥሯል፡፡ ይህ የነበረውን ፍላጎት በማቃናት ድጋሚ መስራትን ይጠይቃል፡፡ ጤናን ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚውንም የሚፈትን ሆኗል፡፡ ኢኮኖሚ በራሱ ሲፈተን እና አንዳች ኃይል ሲፈትነው ይለያያል፡፡ ከ170 በላይ አገራት ዓመቱን ሲጀምሩ ከነበራቸው ዕድገት ሊቀንሱ እንደሚችሉ ዓለማቀፉ የገንዘብ ተቋም አስታውቆ ነበር ፡፡ የዓለም ኢኮኖሚም 9 በመቶ ሊያሽቆለቁል ይችላል ተብሏል፡፡ ይህ አንዳንዶች ላይ ይበረታል አንዳንዶች ላይ መጠኑ ይቀንሳል፡፡ የዓለም ምግብ ድርጅት ከነበረው 135 ሚሊዮን ህዝብ  የሚራበው 265 ሚሊዮን ይደርሳል ብሏል፡፡ እኛም ጋ ለረሀብ የሚጋለጡ ይኖራሉ፡፡

የቱሪዝም ዘርፉ 85በመቶ አሽቆልቁሏል ይህ እኛንም ጎድቶናል፡፡ 90 በመቶ የአየር መንገድ ኢንዱስትሪው ተመቷል፡፡የኮቪድ ጉዳይ ወረርሺኙ ካበቃም በኋላ ጉዳቱ ይቀጥላል፡፡ ከ50 ያላነሱ አገራት ምርጫቸውን አራዝመዋል፡፡
ኮሮና በ3 ዞን ተከፍሎ ይታያል፡-

1. የፍርሀት
2. የመማር
3. ወደ ዕድል የመቀየር

እኛ የመረጥነው ኮሮና አደጋም ቢሆን ወደ ዕድል የመቀየርን ነው፡፡ ለምሳሌ ጤናው ተፈትኗል፡፡ ደቡብ አፍሪካ ናሙና ከመላክ ጀምረን በ3ወር ውስጥ 31 ላቦራቶር ኖሮን በቀን እስከ 8 ሺህ ሰው መመርመር ችለናል፡፡ እስከ ሐምሌ በቀን ከ14 ሺህ በላይ መመርመር እንጀምራለን፡፡ እስካሁን 143 ሺህ በላይ ሳምፕል ተወስዷል፡፤ መንግስት 5ቢሊዮን ብር መድቦ ላቅ ያለ አመራር ወስዷል፡፡

የኢትዮጵያውያንን በሽታ የመከላከል አቅም እንመርምር ለሚሉትም ሆነ መድሀኒት ላይ ለሚመራመሩት አንዱ አንዱን ሳይነካ እንዲሄድ ተደርጓል፡፡ እስከ 17ሺህ 500 ሰዎች በቫይረሱ ቢያዙ የሚታከሙበት 54 የህክምና ማዕከል ተዘጋጅቷል፡፡ 30ሺህ ምልክቱ ለታየባቸው ማቆያ ተዘጋጅቷል፡፡ ለ45 ሺህ ከውጭ ለሚመጡ ማቆያ ተዘጋጅተናል፡፡ ለከፋው ነገርም መዘጋጀት ይጠይቃል፡፡ ይህንን ዝግጁነት በሌሎችም በሽታዎች መድገም ያስፈልጋል፡፡ ለክልሎች ከ400 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጓል ስደተኛ ለሚቀበሉ ክልሎች ልዩ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ኮሮና መንግስታዊ በሽታ አይደለም መንግስት ያወቀውን መረጃ ሁሉ ይፋ አድርጓል፡፡

ኢኮኖሚውን በተመለከተ በዚህ ዓመት 9 በመቶ ለማሳደግ አስበን ነበር ቢያንስ 6 በመቶ ያድጋል፡፡ የኛ ከሌላው ዓለም የተለየ የሆነበት አንደኛው ምክንያት የበጀት ዓመቱ ሐምሌ ላይ በመጀመሩ ነው፡፡ ኮቪድ የመጣው ባለፉት 4 ወራት ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት የንግድ ስርዓታችን ትስስር ከ30 በመቶ በታች መሆኑ ነው፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የካፒታል አካውንታችን ክፍት ባለመሆኑ የፋይናንስ ዘርፉን መከላከል አስችሏል፡፡

ባለፉት 10 ወራት በቁጠባ 17.4 በመቶ እና የባንክ ብድር 24 በመቶ አድጓል፡፡ የተበላሸ ብድርም በግል ባንኮች ከአምናው በ4 በመቶ ቀንሷል፡፡ በልማት ባንክ ከዓምናው 13 በመቶ ቀንሷል፡፡ ይህ ኮሮና እያለ ዝም ብሎ የመጣ አይደለም፡፡ 27 በመቶ ቦንድ አስቀርተናል፡፡ለባንኮች ፈሰስ አድርገናል፡፡ ለአነስተኛና ጥቃቅን በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡ የእዳ ስረዛ አድርገናል፡፡ ከፍተኛ ገንዘብ አፍስሰናል፡፡

የወጪ ንግድን ስንመለከት 13 በመቶ አድጓል፡፡ ቡና ፣አበባ እና ስጋን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በገቢ ንግዱም ነዳጅ ቀንሷል በ100 ሚሊዮኖች የሚገመት ዶላር አትርፈናል፡፡ መድሀኒት ፣ማዳበሪያ፣ የምርት ግብአት ጨምሯል፡፡ በውጭ ምንዛሪ እጥረት ወይም በኮርና የገቢ ንግድ አልቀነሰም ሌሎች የቀነሱ አሉ፡፡ የቱሪዝም፣ አገልግሎት፣ኢንዱስትሪ፣ሆቴሎች እና ትራንስፖርት የመሰሉት ተጎድተዋል፡፡

አገራችንን ከኮቪድ በኋላ የቱሪስት መናገሻ ለማድረግ እየተሰራ ነው፡፡ አዲስ አበባ ላይ የማያሳፍር ያቀድነውን በጊዜው መተግበር እንደምንችል ያሳየንበት ስራ ተሰርቷል፡፡እንጦጦ ትልቅ መስህብ ነው የወንዝዳር ፕሮጀክቱም ሌላ ድህነት እንደሚራገፍ ማሳያ ነው፡፡ ብዙ አቅም አለን ያንን ማውጣት ያስፈልጋል፡፡ ትምህርት ቤቶች እና የእምነት ተቋማት መዘጋታቸው ተፅዕኖ አሳድሯል ያንን ለማካካስ የፀሎት ፕሮግራም በቴሌቪዥን እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡

ከምግብ እጥረት ጋር ተያይዞ ሰፊ ስራ ተሰርቷል፡፡ በ3.2 ቢሊዮን ብር የስንዴና የዘይት ግዢ ተፈፅሟል፡፡ ከመንግስት ውጪ በማዕድ ማጋራት 1.8 ቢሊዮን ብር ርዳታ ተገኝቷል፡፡ ይህንን ባህል ማድረግ ከቻልን ብዙ ቤተሰብ ይታገዛል፡፡ከውጭ 2.2 ቢሊዮን ዶላር ማምጣት ተችሏል፡፡ ዓለማቀፉ የገንዘብ ተቋም እና የዓለም ምግብ ድርጅት ድጋፍ አድርገዋል፡፡ ኢትዮጵያ የዕዳስረዛ እንዲደረግ ለሌሎች የአፍሪካ አገራትም ጭምር የሚተረፍ ስራ ተሰርቷል፡፡ አሁንም ኮሮናን መከላከል ነው የሚያዋጣው አፋችንን እና አፍንጫችንን መሸፈን፣ መታጠብ እና ርቀታችንን መጠበቅ ይገባናል፡፡

ኮሮናም ሆነ መሰል አደገኛ ሁኔታ ሲፈጠር ማንኛውም ሃላፊ ከግብታዊ ርምጃ መቆጠብ አለበት፡፡ ከቻይና ተማሪዎቻችንን መንግስት ያስወጣ የሚል ክስ ይሰማ ነበር፡፡ እኛ ግን ከቻይና መንግስት ጋር ተነጋገርን የገንዘብ ድጎማም አደረግን፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራ ያቁም የሚል ክስም ይሰማ ነበር ፡፡ እንደ ሌሎች አየር መንገዶች ሰራተኛ አልቀነስንም ፤ዕዳውን እየከፈለ ነው ፣የአየር ሊዝም ይከፍላል፡፡ አሁን የህዝብ ትራንስፖርት ቆሟል፡፡ ነገርግን በካርጎ በዓለም ላይ ስመጥር ሆኗል፡፡ ምስጋና ይገባዋል፡፡ በዚህም ቻይና በሳምንት 90 በረራ ፈቅዳለች፡፡ በገንዘብም አግዛለች በችግር ጊዜ ከጎኗ ስለነበርን፡፡ ኮሮናን በተመለከተ እስካሁን የሄድንበት የሚያስመሰግን ሲሆን የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ ሆኖ ምክሮችን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**በ2012/13 የምርት ዘመን የግብርና ግብአት ማቅረብ ፡-** እርሻ የኢኮኖሚው የጀርባ አጥንት ነው፡፡ መሬት ጦም ማደር የለበትም ስንል የግብአት ዝግጅት ይፈልጋል፡፡ በኩታ ገጠም እና በመስኖ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በቆላማ ቦታዎች መስኖ ማስፋፋት በሚል 20 ሺህ ሄክታር አዋሽ ኦሞ እና ሌሎቹንም አልምተናል፡፡ ይህንን በሚቀጥለው ማስፋት ይኖርብናል፡፡ ከቆላ መስኖ በተጨማሪ 10 ሺህ ፓምፖች እያስገባን ነው፡፡ አርሶ አደሩ ማምረት እንዲችል በዚህም የግብርናው ምርት ያድጋል፡፡ 14.6 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ለማስገባት ታቅዷል፡፡ 10.5 ሚሊዮን ኩንታል ክልሎች ጋር ደርሷል፡፡ 1.9 ሚሊዮን ኩንታል እየመጣ ነው፡፡ 2ሚሊዮን ኩንታል ወደ ጅቡቲ እየተጓጓዘ ነው፡፡ ምርጥ ዘር 743 ሺህ ኩንታል ተገዝቷል ግን በቂ አይደለም፡፡ ፀረ አረም ኬሚካልም ተዘጋጅቷል፡፡ የማሳ ዝግጅቱ ተስፋ የሚሰጥ ነው፡፡

**ታዳጊ ተብለው ይጠሩ የነበሩ ክልሎች በአገር ጉዳይ ላይ እኩል እንዲወስኑ ስለማድረግ፡-**
በፖለቲካው ስርአት ውስጥ ቀደም ሲል ዋና እና ተመሪ የሚባል ነበር፡፡ እኩል ተሳትፎ እንዲኖር በተሰራው ስራ ታዳጊ ክልሎች እኩል የሚናገሩ እና የሚደመጡ ሆነዋል፡፡ ከኢኮኖሚ አንፃር ገና ብዙ ስራ መስራት ይጠበቅብናል፡፡ በሶማሌ ክልል ት/ቤቶች እና በአፋር በስንዴ እርሻ የተጀመሩ ጥሩ ውጤት ያላቸው ጅምር ስራዎች ናቸው፡፡

**መንግስት አቅም አንሶታል ስለመባሉ፡-**
ቀደም ሲል ለፖለቲካ ድርጅቶችም ለአዝማሪዎችም ዘፋኞችም ስለኔ ያልተገባ ነገር መናገር አትችሉም ነበር የሚባለው፡፡ አትሙኝ የሚል መንግስት ነው የነበረው፡፡ ይሄ መንግስት ኮሽ ባለ ቁጥር የሚበረግግ አይደለም፡፡ መሰረታዊ የመንግስት ብቃት የሚባሉት ላይ የአፍሪካም ኩራት ነው፡፡ ገናሌ ግድብ ተጠናቆ 3 ዓመት ተቀምጦ ነበር በዓመት በትንሹ 6መቶ ሚሊዮን ብር አጥተናል፡፡ ያንን አለመቻል እና ይሄንን መቻል የቱ ነው ጠንካራ የሚያሰኘው፡፡ ለውጡ ሲመጣ 59 በመቶ ዕዳ ስለነበረብን መበደር የማትችል አገር እንደነበረችን ይታወቃል፡፡ 31በመቶ የውጭ ዕዳ ነበረባት የGDP አሁን ወደ 25 በመቶ ዝቅ አድርገናል።

ይህ ጥንካሬን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ኢንደስትሪ ፓርኮች ተጨርሰዋል፤ ከባህርዳር በስተቀር፡፡ በስኳር ፋብሪካዎች ዘንድሮ ኦሞን ስናሰራ 600 ሺህ ኩንታል ተጨማሪ ማምረት ተችሏል፡፡በለስ ስራው ተሳክቷል፡፡ ስመጣ 86-87 ቢዮን ዶላር ነበር GDP አሁን ከ100 ቢሊዮን በላይ ሆኗል፡፡ የነፍስ ወከፍ ገቢ 880 ዶላር ነበር አሁን ከ1 ሺህ አልፏል፡፡ ይህ የዓለማቀፍ ጥናት ነው ብዙ መተንተን ይቻላል፡፡ ከመቆጣት ጋር ብቻ አናያይዘው ይሄረብ የለሽ ሃሳብ ነው፡፡ የመንግስት አቅም መለኪያ ማቀድ እና ያቀድነውን መፈፀም መሆን አለበት፡፡

**የእንቦጭ አረምን ስለ መከላከል፡-**
እምቦጭን ለመከላከል ሁለት አይነት መከላከያ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡አንደኛው ጊዜያዊ  መፍትሔ ነው፡፡ ይህ ማለት በሰው ሃይል እና በማሽን መጠቀም ለዚህም ሻል ያለ ማሽን ያስፈልጋል፡፡ በፌደራል ደረጃ እየተሞከረ ነው፡፡ ማሽኑ ከ300 ሚሊዮን በላይ የሚጠይቅ ነው፡፡ ዘላቂው መፍትሔ ደግሞ የጉናን ተራራ ከደን መራቆት መጠበቅና ማልማት ነው፡፡ ተከዜን እና ጣናን የሚመግበው የጉና ተራራ እንደመሆኑ ከዚያ ተነስቶ ፎገራን የሚጥለቀልቀው ጎርፍ ያጣናን እምቦጭ ይመግባል፡፡ ስለዚህ ደንን የማልማት ስራን ምክር ቤቱም ሆነ የአማራ ክልል እንደዘላቂ መፍትሔ ሊያየው ይገባል፡፡

**ምርጫ ካልተካሄደ የሽግግር ወይም ባላደራ መንግስት ካልተቋቋመ ስለሚሉ ፓርቲዎች፡-**
ምርጫ ቦርድ የምርጫ አስፈፃሚዎችን አሰልጥኜ ማሰማራት እቸገራለሁ ሲል ከወ/ት ብርቱካን ጋር ባልተለመደ ሁኔታ የቃላት ልውውወጥ አድርገናል፡፡ ብልፅግና ምርጫ የሚያስፈራው ፓርቲ አይደለም፡፡ ወ/ት ብርቱካን አልችልም ሲሉ እንደተፎካካሪ በመቁጠር እናንተ ማሸነፍ ስለማትችሉ ነው ወይ ነበር ያልኳቸው፡፡ይህንን ሃላፊነት የተቀበልኩት የማያሳፍር ምርጫ ለማድረግ ነው ፤የጨረባ ምርጫ የሚደረግ ከሆነ ስራዬን መልቀቅ እችላለሁ እርስዎ ሊያዙኝም ሊቆጡኝም አይችሉም አሉኝ፡፡ ከክቡር አፈጉባኤው ጋር ተነጋገርን፡፡ ዓለም አልችልም ያለውን እኛ እንችላለን ማለት ተገቢ አይደለም፡፡ በህግ ስልጣን ያለው ምርጫ ቦርድ ነው፡፡ ከተወያየን በኋላ የፖለቲካ ውሳኔውም የህግ ውሳኔውም እንዲታይ ማድረግ አለብን በሚል 3 የማይተዋወቅ  ቡድን አደራጀን፡፡ ማሻሻል፤ መተርጎም፤ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ማራዘም እና ፓርላማውን መበተን የሚሉ አራት ሃሳቦች ቀረቡ፡፡ የህገመንግስት ትርጉም የሚለው ተቀባይነት አገኘ፤ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ተመካከርንበት፡፡ ምክር ቤቱ ለትርጉም ለኮሚቴው መራው፡፡

እኛ የበላይ ስልጣንን ውሳኔ የመቀየር አቅም የለንም፡፡ አጣሪ ኮሚቴው ውይይት አካሂዷል፡፡ ይሄ ጥሩ ልምምድ ነው፡፡ ህጉን ለመቀልበስ የሚያስችል ስልጣን ለኛ አልተሰጠንም፡፡ ከምርጫ ቦርድ አንፃር የማይረባ ነገር አንሰራም ማለታቸው ተቋም እየገነባን እንደሆነ ያሳያል፡፡

ሽግግር፣ ምክክር የሚሉ ሀሳቦች ይነሳሉ ግለሰቦች በመሰላቸው መንገድ ሃሳብ ማንሳት አለባቸው፡፡ ሃሳብ ማንሳት መወያየት አይከለከልም ማድረግ ግን አይቻልም ኢ-ህገመንግስታዊ ስለሆነ፡፡ ስለዚህ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ታግሰው ዝግጅት አድርገው ቢጠብቁ እና ኢትዮጵያ ለዴሞክራሲ መሰረት ያላት መሆኗል የሚያሳይ ምርጫ ብናደርግ፡፡ ኮሮና ባይመጣና ምርጫ ብናደርግ ደስ ባለን፡፡ 5ቢሊዮን ችግኝ መትከል ከቻልን ለምን ምርጫ አናደርግም የሚሉም አሉ፡፡ ትስስር የለውም፡፡ ምርጫ አስፈፃሚዎችን ማሰልጠን ይፈልጋል፤ ከአንድ ቀኑ ድምፅ መስጠት በፊት ብዙ ዝግጅትም ይጠይቃል፡፡ ችግኝ መትከል በግል የሚደረግ በተፈለገ ጊዜ ባሉት ዘጠና ቀናት የሚከናወን ነው፡፡

**የህዳሴውን ግድብ አዲሱ አመራር ለድርድር አቅርቦታል ስለመባሉ፡-**
ግድቡ ለድርድር ቀርቧል የሚለው አሉባልታ ለምክር ቤቱ አይመጥንም፡፡ ግልፅነት እንዲፈጠር ከሆነ ግድቡ በተያዘለት ጊዜ በ2009 ዓ.ም አልቆ ቢሆን ድርድር ላይ አንደርስም ነበር፡፡ 6 ዓመት ነው የዘገየው 6ቢሊዮን ዶላር ኪሳራ አድርሷል፡፡ በየጊዜው የምንመግበውን ዩሮ አይመለከትም፡፡ በቁንፅል አንየው፡፡ ፕሮጀክቱ በዕውቀት ፣በሞያ በአሰራር 8 ኮንትራት አለው 6 ኮንትራክተሮች ይሰሩታል፡፡ አንዱ ቢያዘገየው የአምስቱ መስራት ሙሉ አያደርገውም፡፡ ሁሉም ተሰናስለው መስራታቸውን ማየት ይጠይቃል፡፡ አቶ ክፍሌ ጊቤ ላይ ነበሩ ህዳሴ ግድብንም ያስጀመሩ ናቸው፡፡ የአመራር ብቃት ይጠይቃል፡፡ ዋናው ነገር ቴክኒካል ስራው ነው፡፡ የውሃ ሙሌትን በተመለከተ ደን ምንጣሮው ካልተሰራ ውሃ አይያዝም፡፡ ዲፕሎማሲው ቀላል ነው፡፡ እየተሰራ ስለሆነ ዲፕሎማሲው እንዳሁን ከብዶ አያውቅም፡፡

ከጥንስሱ የጀመሩ ፣ያጠኑ፣ ያቀረቡ አቶ አለማየሁ ተገኑ፣ አቶ ግርማ ብሩ እና አቶ ምህረት ደበበ ያጠኑትን ጥናት መለስ ብለን ለማየት ሞክረናል፡፡ ነገሩ የተበላሸው እነሜቴክ ሲገቡ ነው፡፡ ልምድ እና ብቃት ማየት ነበረብን፡፡ አሁን በሳምንት 2 ጊዜ ሪፖርት ይቀርባል፡፡ በቅርብ ክትትል እየተሰራ ነው፡፡ ስህተትን አርመናል፡፡ ህዳሴ ያለበት ቦታ 500 ሜትር ከፍታ ያለው ነው፡፡ ኤሌክትሮ ሜካኒካል የሚሰራበት ሜቴክ የያዘው ክፍት ነበር፡፡ ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል ተጨማሪ 35 ሜትር በመስራት 65 ሜትር እያደረስነው ነው፡፡ ይህ የሲቪል ስራው ነው ኤሌክትሮ ሜካኒካል ስራው እንደ አዲስ ነው የተሰራው፡፡ በሰኔ ወር 4.9 ቢሊዮን ኪዮቢክ ሜትር ውሃ እንይዛለን፣ 595 ሜትር ስናደርስ 18.4 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር እንይዛለን፣ 640 ሜትር ከመሬት በላይ ስንደርስ 74 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ እንይዛለን፡፡4.9 ኪዩቢክ መያዙ ነው ከባድ እና  አነጋጋሪው፡፡ 140 ሜትር ርዝመት አለው፡፡ ከለውጡ በኋላ 115 ሜትር ሲቪል ይሰራል፡፡ ህዳሴ እንዴት ከሞት እንዳገገመ ይታያል፡፡ እንዲያውም ለውጡ የመጣው ለህዳሴው ነው፡፡ ዲፕሎማሲን በተመለከተ ኢትዮጵያ ማደግ ትፈልጋለች ከልመና መውጣት ትፈልጋለች፡፡ በቁጥር ብዙ ነን

ወደብ የለንም፡፡ ከ50 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ንፁህ መጠጥ ውሃ አያገኝም 50 ሚሊዮን ህዝብ መብራት የለውም እናቶች በጀርባቸው እንጨት ይሸከማሉ ፡፡ይሄ እንዲያበቃ ነው የምንፈልገው፡፡ ልባም ጎረቤቶች ካሉን ማገዝ አለባቸው፡፡ በህዳሴ ግድብ ማንም አይጎዳም፡፡ በዚህ ላይ ጠ/ሚሩ ብቻ እንደሚደራደሩ መቁጠር የባለሞያዎችን ሞራል ይጎዳል፡፡ለውጡ ባለሞያዎቹን ይዞ ነው የቀጠለው፡፡ በድርድር ህዳሴን መሸጥ ይከብዳል፡፡

**የሱዳን ወታደሮቿን ድንበር ላይ ማስጠጋት፡-**

የሱዳን ህዝብ ወንድም ህዝብ ነው በጣሊያን፣ በ77ድርቅ እና በቀይ እና ነጭ ሽብር ዘመን የኢትዮጵያ ባለውለታ ነው፡፡ ካርቱም አሁንም በርካታ ኢትዮጵያውያን አሉ፡፡ ከሱዳን ጋር ካልተዋጋችሁ የሚሉ ኃይሎች የሉም ማለት አይቻልም፡፡ የሱዳን ህዝብ የዚህ ፍላጎት የለውም ሰፊ ንግግር እያደረግን ነው፡፡ የድንበር ጉዳይ ከሆነ ከግብፅ ጋር ሰፊ ድንበር አላቸው፡፡ በድርድር የሚፈታ ጉዳይ ነው ማጋጨት የሚፈልጉ ቢኖሩም፡፡

**የአምነስቲ ሪፖርት፡-**

ማንኛውም ድርሰት እና ሪፖርት ተደራሲ እና ደራሲ አለው፡፡ የኢትዮጵያውያን መብት እየተጎዳ ነው ካለ ትምህርት መውሰድ አለብን፡፡ እኛን የሚዳኘን የኢትዮጵያ ህዝብ ነው፡፡ ፈትሾ ማስተካከል ተገቢ ነው፡፡

**በትግራይ ህዝብ ላይ አድልዎ ተፈፅሟል፡፡ የባቡር መስመር እና ሌሎቹም ቆመዋል፡፡ ሚዲያዎቹም ትግራይ ላይ ዘመቻ እያካሄዱ ነው፡-**

የትግራይ ህዝብ ጀግና ፤ በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ ፤ጥሮ ግሮ የሚበላ ጋሻ ህዝብ ነው፡፡ ችግር እየሆነ ያለው ፓርቲዎችን እና ህዝብን ማቀላቀል ነው፡፡ትግል ሲጀመር ኢ.ዲ.ዩ፣ ጠርናፊት፣ ህወሀት፣ ታሀት፣ ኢህአፓ ነበሩ፡፡ ዛሬም አረና፣ ባይቶና ፣ሳልሳይ ወያነ፣ ህወሀት፣አሲምባ ፣ ብልፅግና ውስጥም ያሉ አሉ፡፡ ለይቶ ማየት ያስፈልጋል፡፡

ሁሉም ጥፋተኛ ነው የሚል ሀሳብ የለንም፡፡ ብዙ አካል ጉዳተኞች አሉ፡፡ የክልሉ አመራርም ሰላምን የሚፈልግ ነው፡፡ ጥፋተኞች የሉም ማለት ግን አይደለም፡፡ ደምረን ግን ትግራይ ማለት አያሰኝም፡፡ አንድ ሰው ሲወቀስ የትግራይ ህዝብ አንበለው፡፡ በህወሀት እና በሌሎች ፓርቲዎች ንግግሮች አሉ፡፡ ይህንን መቀነስ ይሻላል፡፡ ሚዲያን በሚመለከት ዐብይን ለመሳደብ የተቋቋሙ ሚዲያዎች አሉ፡፡ ስድብ የኢትዮጵያን ብልፅግና ስለማያቆም ቦታ አንሰጠውም፡፡ እኔስመጣ የትግራይ በጀት 7ቢሊዮን ብር ገደማ ነበር አሁን 10.4 ቢሊዮን ሆኗል በ42በመቶ አድጓል፡፡ ለውጡ ለትግራይም የመጣ ነው፡፡ ቁጥጥር የሚያደርገው የክልል ም/ቤት ነው፡፡ ብዙ ዘመቻዎች አሉ፡፡ እንደ ህዳሴው ሁሉ አቧራ ነው አሻራ መሆን አይችልም፡፡ በኮሮና ብቻ 46 ሚሊዮን ብር ትግራይ ተረድቷል፡፡ ለማዳበሪያ ትግራይ እና ደቡብ የነበረባቸውን ዕዳ አልከፈሉም፡፡ 445ሚሊዮን ብር የፌደራል መንግስት ተበድሮ ማዳበሪያው እንዳይቀር ተደርጓል፡፡ ለመቀሌ ውሃ ከ9 ቢሊየን ብር በላይ ነው የተፈራረምነው፡፡ አንጀምርም ስላሉ 1.3 ቢሊዮን ብር ነው ዘንድሮ የከፈልነው፡፡ ህዝቡ ስለሚገባው እና መደረግ ስላለበት፡፡

የወልዲያ መቀሌ ባቡር ትንሽ ችግር አለበት፡፡ የአንድ ኪሎሜትር ዋጋ በጣም ውድ ነው፡፡ 40 በመቶ በኢትዮጵያ እና 60 በመቶ በኤግዚም ባንክ ነበር ሊሰራ የነበረው ኤግዚም ባንክ አላበድርም አለ፡፡ ሌሎቹንም ሞከርን አናበድርም አሉ፡፡ ከዚህ ጋር የታሰቡ ከአዲስ አበባ አምቦ እና ከአዲስ አበባ ጅማ ፕሮጀክቶች አልተፈረሙም፤ ታሰቡት እኩል ነው፡፡ የአምቦ ህዝብ በደል ተፈፀመብኝ አላለም፡፡ በፍፁም ወደ መቀሌ ባቡር እንዳይገባ የሚሰራ መንግስት የለም፡፡ ብልፅግና ትንንሽ ነገር አይመቸንም፡፡ ከፍ ያለ ነገር እናስባለን፡፡

በGTP 2 ትግራይ ውስጥ የተያዙ 23 የመንገድ ፕሮጀክቶች አሉ፤ ብዙዎቹ እየተሰሩ ነው፡፡ መንገድም፣ ባቡርም ውሃም እንሰራለን ህዝቡ ስለሚገባው፡፡ ይህ የሚታይ ስለሆነ ብታዩት፡፡

//